የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

**OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA**

ሰላሳ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፹፯
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ/ም

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32th Year No.87
Addis Ababa 28th day of Jun, 2024


**ማውጫ**


**ደንብ ቁጥር ፻፸፯/፪ሺ፲፮**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቀዳማይ ልጅነት ልማት ልሕቀት ማዕከል ማቋቋሚያ ማሻሻያ ደንብ**

**ገፅ.............................................፫ሺ፯፻፴፮**


**CONTENTS**


**Regulation Number 177/2024**

**The Ababa City Administration Early Childhood Development Center of Excellence Establishment Amendment Regulation**

Page ………………….………….…………… 3736


**ደንብ ቁጥር ፻፸፯/፪ሺ፲፮**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቀዳማይ ልጅነት ልማት ልሕቀት ማዕከል ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፻፵፪/፪ሺ፲፬ን ለማሻሻል የወጣ ደንብ**

አዲስ አበባ ከተማ ህፃናትን ለማሳደግ ምርጥ የአፍሪካ ከተማ ለመሆኗ ራዕይ ይዛ በቀዳማይ የልጅነት እንክብካቤና እድገት ትግበራ ረገድ በአገር አቀፍ፣ በአህጉር፣ እንዲሁም በአለም አቀፍ ደረጃ የተሞክሮ ማእከል ለመሆን እየሰራች ያለች በመሆኑዋ የቀዳማይ ልጅነት ልማት ልሕቀት ማዕከሉን ስያሜ አህጉራዊ ስያሜ እንዲኖረው ደንቡን ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር ፹፬/፪ሺ፲፮ አንቀፅ ፺፬ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን ማሻሻያ ደንብ አውጥቷል፡፡

**Regulation Number 177/2024**

**A Regulation to provide for the Amendment of regulation No. 142/2022 issued for the Addis Ababa City Administration Early Childhood Development Center of Excellence Establishment Regulation**

WHEREAS, it has been found necessary to amend the regulation to make the name of the center of Excellence for Early Childhood Development have a continental name as the city Administration has been a vision to be the best African city for raising children and working towards becoming a center of experience in the implementation of early childhood care and development at the country and continent level.

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 94 of the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment to re-specify the power and duties of the thereof Proclamation No. 84/2023, the Cabinet of Addis Ababa City Government has issued this Regulation.


ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
**Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445**

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ ደንብ «አፍሪካ የቀዳማይ ልጅነት ልማት ልሕቀት ማዕከል ማቋቋሚያ (ማሻሻያ) ደንብ ቁጥር ፻፸፯/፳፻፲፮/» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>ትርጉም</u>**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. **“ደንብ”** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቅድመ ልጅነት ልማት ልህቀት ማዕከል ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፻፵፪/፳፻፲፬ ነው፤

፪. በደንቡ ውስጥ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላትና ሐረጎች ለዚህም ደንብ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**፫. <u>ማሻሻያ</u>**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቅድመ ልጅነት ልማት ልህቀት ማዕከል ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፻፵፪/፳፻፲፬ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩. የደንቡ አንቀጽ ፩ ተሰርዞ በአዲስ አንቀጽ ፩ ተተክቷል፡-

« **፩ <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ ደንብ «አፍሪካ የቀዳማይ ልጅነት ልማት ልሕቀት ማዕከል ማቋቋሚያ (ማሻሻያ) ደንብ ቁጥር ፻፸፯/፳፻፲፮/» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡"

፪. በደንቡ ውስጥ በማናቸውም ስፍራ «የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቅድመ ልጅነት ልማት ልህቀት ማዕከል» የሚለው ስም ተሰርዞ «የአፍሪካ የቀዳማይ ልጅነት ልማት ልሕቀት ማዕከል» በሚል ተተክቷል፤

**1. <u>Short Title</u>**

This Regulation may be cited as: “Africa Early Childhood Development Center of Excellence Establishment (Amendment) Regulation No177/2024.”

**2. <u>Definition</u>**

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1. **“Regulation”** means the Addis Ababa City Government Early Childhood Development Center of Excellence Establishment Regulation No 142/2022.”;
2. The words and phrases defined in the regulation shall also be applied in this regulation.

**3. <u>Amendment</u>**

Regulation No. 142/2022 that was issued for the Establishment of the Addis Ababa City Government Early Childhood Development Center of Excellence is hereby amended as follows.

1. Article 1 of the regulation has been deleted and replaced with the following new Article 1;

"**1. <u>Short Title</u>**

This Regulation may be cited as: “Africa Early Childhood Development Center of Excellence Establishment (Amendment) Regulation No177/2024.”

2. In any Article in the Regulation, the name "Addis Ababa City Government Early Childhood Development Center of Excellence" has been deleted and replaced with "African Early Childhood Development Center of Excellence".

፫. የደንቡ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዞ በአዲስ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፡-

«፫. *መቋቋም*

፩. አፍሪካ የቀዳማይ ልጅነት ልማት ልህቀት ማዕከል "ከዚህ በኋላ የልህቀት ማዕከል ተብሎ የሚጠራ" ሕጋዊ ሰውነት ያለው አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤"

፬. **የመብትና ግዴታ መተላለፍ**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቅድመ ልጅነት ልማት ልህቀት ማዕከል መብትና ግዴታ ለአፍሪካ የቀዳማይ ልጅነት ልማት ልህቀት ማዕከል ተላልፏል፡፡

፭. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከሰኔ ፳፩ ቀን ፪፲፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**አዳነች አቤቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

3. Sub Article (1) of Article 3 of the Regulation has been deleted and replaced with the following new Sub Article (1);

"**3. Establishment**

1. The Africa Early Childhood Development Center of Excellence (hereinafter the "Center of Excellence") is hereby established as an autonomous Addis Ababa City Administration executive body having its own legal personality.

**4. Transfer of Right and Obligation**

The right and obligation of the Addis Ababa Government City Early Childhood Development Center of Excellence is hereby transferred to the Africa Early Childhood Development Center of Excellence.

**5. Effective Date**

This Regulation shall enter into force as of this Jun 28th, 2024.

**Done at Addis Ababa, this Jun 28th, 2024**

**Adanech Abiebie**

**Mayor of Addis Ababa City**